# የተሽከርካሪ የደህንነት ቀበቶ በተሽከርካሪ ወንበሮች ላይ እንዲኖር እና ተግባራዊ እንዲደረግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 44/2013

## 1. መግቢያ

የመንገድ ትራንስፖርት ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገት የማይተካ ሚና እንዳለው የሚካድ አይደለም:: ሚናውንም ደህንነቱ የተጠበቀ ለማድረግ በቴክኖሎጂ የተደገፈና በህግ ማዕቀፍ ውስጥ የተቀመጠ መሆን ይኖርበታል:: ከነዚህም መንገዶች ውስጥ በማንኛውም እንቅስቃሴ የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎችን መጠቀም ወሳኝ ነው:: የአለም የጤና ድርጅት እንዳወጣው መረጃ በህዝብ ትራንስፖርት አማካኝነት የሚንቀሳቀሱ አካላት በጉዞ ወቅት የደህንነት ቀበቶ በአግባቡ ቢጠቀሙ አደጋ በሚያጋጥማቸው ወቅት አሽከርካሪውንና ከፊት የሚቀመጡ አካላት ከ45 እስከ 50% ለሞት ተጋላጭነታቸውን እንደሚቀንስና ከኃላ የሚቀመጡ ተጓዦችን ደግሞ ከ25 እስከ 35% ከሞት ሊደጋቸው እንደሚችል ያሳያል::በሃገራችንም በደህንነት ቀበቶ ምክንያት የደረሱ አደጋዎች ጥናት ተደርጎባቸው የተቀመጡ ባይሆንም ለአደጋዎቹ አስከፊነት የደህንነት ቀበቶን አለመጠቀም ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው የማይካድ ነው::

በደንብ ቁጥር 208/2003 እና በማሻሻያው 395/2009 ተራ ቁጥር 5 ጠቅላላ የጥንቃቄ መርሆች አንቀፅ ቁጥር 3 ከ ሀ እስከ ሐ እንዳስቀመጠው ማንኛውም አሽከርካሪ ከሞተር ብስክሌት በቀር የደህንነት ቀበቶ ሳያስር በመንገድ ላይ ማንኛውንም ተሽከርካሪ ማሽከርከር እንደሌለበት፤ ማንኛውም አሽከርካሪ በሚያሽከረክርበት ወቅት በተሽከርካሪው ውስጥ የተሳፈረው ሰው የደህንነት ቀበቶ ማሰሩን ማረጋገጥ እንዳለበትና በንዑስ አንቀፅ ለ (ማንኛውም አሽከርካሪ በሚያሽከረክርበት ወቅት በተሽከርካሪው ውስጥ የተሳፈረው ሰው የደህንነት ቀበቶ ማሰሩን ማረጋገጥ እንዳለበ)ድንጋጌ ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ተሽከርካሪዎችን በሚመለከት ባለስልጣኑ እንደሚወስን ይደነግጋል:: ስለሆነም የደህንነት ቀበቶ ባለማሰር ምክንያት የሚደርሰውን አደጋ ለመከላከልና ለመቀነስ ባለስልጣን መስሪያቤቱ ይህንን መመሪያ አዘጋጅቷል::

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የተሽከርካሪ የደህንነት ቀበቶ በተሽከርካሪው ወንበሮች ላይ እንዲኖር እና ተግባራዊ እንዲደረግ የወጣ መመሪያ ቁጥር **44/2013** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በመመሪያው ውስጥ የቃሎቹ ትርጉም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

- 2.1. **ባለስልጣን** ማለት የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ማለት ነው፡፡
- 2.2. **ደንብ** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 208/2003 እና ማሻሻያው ደንብ ቁጥር 395/2009 ነው፡፡
- 2.3. **የትራንስፖርት ቢሮ**ማለት ትራንስፖርትን ለመምራት ስልጣን የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ነው፡፡
- 2.4. **የሚመለከተው አካል** ማለት የደህንነት ቀበቶ በተሽከርካሪው ላይ እንዲኖር የሚፈቅደው ስልጣን ወይም ውክልና ያለው አካል ነው፡፡
- 2.5. **የደህንነትቀበቶማለት፡-**ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የተዘጋጀና በተሽከርካሪው ወንበሮች ላይ የሚገጠም ሲሆን የአሽከርካሪውንና የተሳፋሪዎችን ትከሻ ወይም መቀመጫ ከወንበሮች ጋር የሚያያይዝ ነው፡፡

3. **ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማ በተሽከርካሪዎች ላይ የደህንነት ቀበቶ እንዲኖር በማድረግ ቀበቶ ባለማሰር በአሽከርካሪዎችና በተሳፋሪዎች ላይ የሚደርሰውን የከፋ የመንገድ ትራፊክ አደጋ መቀነስ ነው፡፡

4. **አስፈላጊነት**

- የደህንነት ቀበቶ ማሰር አሽከርካሪው ወይም ተሳፋሪው አደጋዎች በሚከሰቱበት ወቅት በፊተኛው ወይም በጎን ባሉ የተሽከርካሪው መስታወቶች ተስፈንጥረው እንዳይወጡና ይደርስ የነበረውን ከፍተኛ አደጋ ለመቀነስ ያስችላል፡፡
- አሽከርካሪዎች ተሽከርካሪውን ለመቆጣጠር እንዲችሉ ያስችላል፡፡
- አደጋ በሚከሰትበት ወቅት አሽከርካሪውና ተሳፋሪዎች ተሽከርካሪው ውስጥ ካሉ ግዑዝ ነገሮች ጋር ከመጋጨት ይታደጋል፡፡

5. **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ በባለስልጣኑ በሚወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በተመረጡ የመንግስት፣ የግል፣ የጭነትና የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡

# ክፍል ሁለት

## የተለያዩ አካላት ኃላፊነት

2. የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ኃላፊነት

2.1. በሃገሪቱ የሚገኙ ተሽከርካሪዎች አይነት እና መጠን ያማከለ የደህንነት ቀበቶ ዲዛይን መስፈርት ያወጣል፡፡

2.2. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የደህንነት ቀበቶ አጠቃቀም ስርዓትን ለመንገድ ተጠቃሚዎች ያስተዋውቃል፡፡

2.3. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተመረጡ የመንግስት፣ የህዝብ፣ የግል መጠቀሚያ እና የጭነት ተሽከርካሪዎች ላይ ለአሽከርካዎችና ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ ያላቸው ወንበሮች ብቻ መሆን እንደሚገባቸው መመሪያ ይሰጣል፡፡

2.4. የባለስልጣን መስሪያቤቱ በተሽከርካሪ ማስገቢያ ሰነድ ላይ በጉምሩክ በኩል ወደ ሃገር የሚገቡ ተሽከርካሪዎች በሁሉም ወንበሮች ላይ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ባወጣው ዲዛይን እና ደረጃ የደህንነት ቀበቶ ያላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ስህተት የተገኘበት ተሽከርካሪም በመመሪያው መሰረት ማስተካከያ እንዲደረግበት ይቆጣጠራል፡፡

2.5. ተሽከርካሪዎች አመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ሲያደርጉ በአምራች ድርጅቱ በተገጠመላቸው ወንበር ልክ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ባወጣው ዲዛይን እና ደረጃ የደህንነት ቀበቶ መኖር አስገዳጅ መሆኑን መመሪያ ይሰጣል፡፡ይህንንም ለቴክኒክ ምርመራ ተቋማት ያሳውቃል፡፡

2.6. የባለስልጣን መ/ቤቱ በተሽከርካሪዎች ላይ የተገጠመው የደህንነት ቀበቶ በወጣለት መስፈርት ልክ መሆኑን እና በተገቢው አጠቃቀም መፈጸሙን ይቆጣጠራል፡፡

2.7. ባለስልጣን መ/ቤቱ የደህንነት ቀበቶ አተገባበር ላይ የሚታዩ ስህተቶችን እና ዝንፈቶች በተመለከተ የሚወሰዱ የአስተዳደር እርምጃዎችን እና ቅጣት በተመለከተ ተጨማሪ የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣል፡፡

2.8. የደህንነት ቀበቶ አተገባበር ቁጥጥርን በተመለከተ ባለስልጣኑ በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት እንደ አስፈላጊነቱ በውክልና ወይንም በቅንጅት የሚከናወንበትን መንገድ ይነድፋል፡፡

2.9. በሁሉም የሃገሪቱ ክፍል የደህንነት ቀበቶ አተገባበር ወጥነት ባለው መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ያከታተላል፤ ለአፈጻጸሙ መሳካትም ድጋፍ ያደርጋል፡፡

3. በየተዋረዱ የሚገኙ የክልል ትራንስፖርት ባለስልጣን እና የትራንስፖርት ቢሮዎች ኃላፊነት

3.1. በኃላፊነት በሚያስተዳድሩት አካባቢ የትራንስፖርት ባለስልጣን የአፈፃፀም መመሪያ ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ነባር ተሽከርካሪዎች በተቀመጠው መስፈርት ለሁሉም ወንበሮች የደህንነት ቀበቶ እየገጠሙ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ያስፈጽማል፡፡

3.2. በትራንስፖርት ቢሮዎቹ የኦፐሬሽን ፍቃድ የሚሰጣቸው የመካከለኛ እና አነስተኛ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ለሙሉ መንገደኞች እና ሰራተኞች የደህንነት ቀበቶ እንዲገጥሙ ይቆጣጠራል ይከታተላል፡፡

3.3. የደህንነት ቀበቶ አተገባበር ቁጥጥር በውክልና ወይንም በቅንጅት ያከናውናል፡፡ስህተት ባገኙበት ተሽከርካሪ ላይም በደንብ ቁጥር 208/2003 እና በማሻሻያው 395/2009 ተራ ቁጥር 5አንቀጽ 3 ከ ሀ እና ለ እንዳስቀመጠው ማንኛውም አሽከርካሪ ከሞተር ብስክሌት በቀር የደህንነት ቀበቶ ሳያስር በመንገድ ላይ ማንኛውንም ተሽከርካሪ ማሽከርከር እንደሌለበት፤ ማንኛውም አሽከርካሪ በሚያሽከረክርበት ወቅት

በተሽከርካሪው ውስጥ የተሳፈረው ሰው የደህንነት ቀበቶ ማሰሩን ማረጋገጥ ያለበት ሲሆን በዚሁ መሰረት እርምጃ ይወስዳሉ፡፡

3.4. በትራንስፖርት ቢሮዎቹ የደህንነት ቀበቶ አተገባበር መመሪያ አፈጻጸም የስራው አካል ይሆናሉ፡፡

3.5. የትራንስፖርት ቢሮዎች የደህንነት ቀበቶ አተገባበር መመሪያ እና አፈጻጸም ዙርያ ለአሽከርካሪዎች፣ ለመንገደኞች፣ ለትራንስፖርት ማህበራት፣ ለተሽከርካሪ ባለንብረቶች፣ ለህግ አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም ለማኝኛውም ትራንስፖርት ተጠቃሚ ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡

## 4. የፌደራል እና የክልል ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ ኃላፊነት

4.1. የደህንነት ቀበቶ አተገባበር ቁጥጥር በውክልና ወይንም በቅንጅት ያከናውናል፡፡ስህተት ባገኙበት ተሽከርካሪ ላይም በደንብ ቁጥር 208/2003 እና በማሻሻያው 395/2009 ተራ ቁጥር 5አንቀጽ 3 ከ ሀ እና ለ እንዳስቀመጠው ማንኛውም አሽከርካሪ ከሞተር ብስክሌት በቀር የደህንነት ቀበቶ ሳያስር በመንገድ ላይ ማንኛውንም ተሽከርካሪ ማሽከርከር እንደሌለበት፣ ማንኛውም አሽከርካሪ በሚያሽከረክርበት ወቅት በተሽከርካሪው ውስጥ የተሳፈረው ሰው የደህንነት ቀበቶ ማሰሩን ማረጋገጥ ያለበት ሲሆን በዚሁ መሰረት እርምጃ ይወስዳሉ፡፡

4.2. በደህንነት ቀበቶ አተገባበር ቁጥጥር ስራ ላይ በተመለከተ መደበኛ ሪፖርት በየደረጃው ለትራንስፖርት ቢሮ አጠናቅረው ያቀርባሉ፡፡

## 5. የተሽከርካሪው ባለቤት ኃላፊነት

5.1. የነባር ወይም የአዲስ ተሽከርካሪ ባለንብረት በአግባቡ የሚሰራ የደህንነት ቀበቶውን በተሽከርካሪው ላይ ማሟላት አለበት፡፡

5.2. የደህንነት ቀበቶው በተገቢው ሁኔታ የሚያገለግል መሆኑን በየጊዜው ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 6. የአሽከርካሪው ኃላፊነት

6.1.አሽከርካሪው የደህንነት ቀበቶውን በአግባቡ ማድረግና ተሳፋሪዎችም በአግባቡ ማድረጋቸውን በራሱና በረዳቱ በኩልያ ረጋግጣል፡፡

6.2.በአግባቡ የሚሰራ የደህንነት ቀበቶ የሌለው ተሽከርካሪ ማሽከርከር የለበትም፡፡

## 7. የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ኃላፊነት

ማንኛውም የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋም፡-

7.1. በዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ወቅት የአሽከርካሪውና የተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ በአግባቡ የሚያገለግል መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

# ክፍል ሶስት

## 3. የደህንነት ቀበቶ የሚገጠምላቸው ተሽከርካሪዎች አይነት

3.1. ነባር(በስራ ላይ ያሉ) እስከ150(አንድ መቶ ሃምሳ)ኪሎሜትር የሚጓዙ ሚኒባሶች እና የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች፣ ከ5 እስከ 8 መቀመጫ ያላቸው ተሽከርካሪዎች፣ ረጅም ርቀት የሚገጓዙ ልዩ ባሶችና ሀገር አቋራጭ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በዚህ መመሪያ ላይ ለአሽከርካሪውና ለሁሉም ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ እንዲኖራቸው የሚወስን ሲሆን ለግል አገልግሎትም የሚጠቀሙ አውቶሞቢሎች የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ ቦርድ ያለው ማካተት አለባቸው፡፡

3.2. በመመሪያ ቁጥር 3.1የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ የጭነት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች፣ ከ12 እስከ 15 ሰው የሚጭኑና በከተማ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ፣ የብዙሃን አገልግሎት የሚሰጡ የከተማአውቶሶች ለአሽከርካሪውና ፊት ወንበር ላይ ለሚቀመጡ ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ እንዲኖረና እንዲጠቀሙ የሚደነግግ ሲሆን ከኃላ ለሚቀመጡ በብዙሃን ትራንስፖርት ቆመው የሚጓዙ እና አጭር ርቀት የሚጓዙ ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ እንዲኖራቸው አያስገድድም፡፡

3.3. በመንግስትና በግል ለሰራተኞች የሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎችም በመመሪያው መሰረት ለአሽከርካሪውና ለሁሉም ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ መኖርና መጠቀም አለባቸው፡፡

3.4. በአስመጪዎች ለሚገቡ አዲስ የመንግስት፣ የግል፣ የህዝብና የጭነት ተሽከርካሪዎች በባለስልጣኑ መ/ቤት በሚወጣው ስፔስፊኬሽን መሰረት ወደ ሃገር የሚገቡ ለአሽከርካሪውና ለተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ የገጠመላቸው መሆን አለበት፡፡

## 4. መመሪያው ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ተሽከርካሪዎች

የዚህ መመሪያ ድንጋጌ ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ተሽከርካሪዎች ከታች የተጠቀሱት እንዳለ ሆኖ አሽከርካሪውና ከፊት የሚቀመጡ የደህንነት ቀበቶ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

4.1. ባለሁለትና ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎች

4.2. በግዳጅ ስራ ላይ ለተሰማሩ ፖሊሶችና የመከላከያ ሰራዊት

## 5. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

የዚህን መመሪያ ድንጋጌ የሚቃረን ማንኛውንም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 6. መመሪያውን ስለማሻሻል

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለስልጣኑ መመሪያውን ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 7. ቅጣትን በተመለከተ

በደንብ ቁጥር 208/2003 እና በማሻሻያው 395/2009 ተራ ቁጥር 5 ጠቅላላ የጥንቃቄ መርሆች አንቀፅ 3 ከ ሀ እና ለመሰረት አሽከርካሪው የደህንነት ቀበቶ ሳያደረግ እና ተሳፋሪዎች ማድረጋቸውን ሳያረጋግጥ የሚያሽከረክር ከሆነ ደንቡ ላይ በተቀመጠው መሰረት የሚቀጣ ሲሆን በሌላ በኩል በዚህ መመሪያ መሰረትም የተሽከርካሪው ባለቤት በተሽከርካሪው ሁሉም ወንበሮች ላይ ደረጃውን የጠበቀ የደህንነት ቀበቶ የማያስገጥም ከሆነ 5000 ብር የሚቀጣ ይሆናል፡፡

## 8. ይህ መመሪያ ከ---------- ቀን-----------ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡